# የጠበል ፎክሎራዊ ገጽታ
# በጨፋ/በጎንዴ ጠበል ማሳያነት

ፍሬህይወት ባዩ


**አጠቃሎ**

ይህ ጥናት ያተኮረው በጨፋ ጠበል ፎክሎራዊ ክዋኔ ላይ ነው። በተለምዶ ጠበሉ የፈለቀበት አካባቢ በሚጠራበት ስም የጨፋ/የጎንዴ ጠበል በመባል ይታወቃል። በኦሮሚያ ክልል በአርሲ ዞን ሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ይገኛል። ጥናቱ የፎክሎርን የጥናት መስክ መሠረት አድርጎ ከ2005 እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ በተለያየ ጊዜ በቃለ-መጠይቅና በምልከታ በተገኘ መረጃ ላይ ተመሥርቶ የተከናወነ ነው። የጠበሉ መፍለቅ ለጨፋ መድሀኒዓለም ደብረቁስቋም፣ ቅድስት ማርያም ወሰሎሜ አንድነት ገዳም መመሥረት ምክንያት ሆኗል። በጠበሉ የሚገለገሉት የእስልምናና የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች ሲሆኑ ጠበል ለመነከርና ለመጠጣት የሚመጡት የጤና መታወክ የደረሰባቸው ግለሰቦች ናቸው። የውሀ ምንጩ ከተራ ውሃነት ወደ ተቀደሰ ውሃነት የተቀየረው በራእይ አማካይነት ነው። ራእይ አንዱ የሚት ጥናት ትኩረት ነው። ከራእዩ ተረኩ ተገነባ። ተረኩ እምነትን መሠረተ። ራእዩ ሁለት ቤተ-ክርስቲያን ተሰርቶ ገዳም እንዲገደም ምክንያት ሆነ። ይህ ራእይ እንዲሁም ትረካ ለአማኙ ማህበረሰብ የተቀደሰ ትረካ ይሆናል። ለማያምንበት ደግሞ እንደ አተያዩ የተለያየ ትርጉም ወይም ሀቲት ሊሰጠው ይችላል። ትረካው በቃል ከአንዱ ወደ ሌላው እየተላለፈ እምነቱ እየሰፋ የጠበል ተጠማቂው ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ከሀያ ሶስት አመት በላይ ሆኖታል። ተጠማቂዎቹ ለጠበል አጠማመቁ በልማድ ብቻ ደንብ አውጥተውለታል። እያንዳንዱ የጠበሉ ተጠማቂ ስለ ጠበሉ በተለይ ከህመሙ ስለማዳኑ የሚተርካቸው ግለ ታሪኩ “ጠበል ያድናል” የሚለውን እምነት የሚተክሉ ናቸው። በጥቅሉ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በጠበል ምክንያት የተገናኙ ማህበረሰቦች እምነት፣ አተያይ፣ ሃይማኖት ያልገደበው ማህበራዊ መስተጋብር የሚታይበት ነው።


## 1.መግቢያ

ጸበል/ጠበል[1] የግእዝ ቃል ሲሆን፣ ጠበልና ጸበል በልሳንና በመሠረታዊ ትርጉም ልዩነት ያላቸው ቢሆንም በሃይማኖታዊ እምነት ባላቸው አገልግሎት በተወራራሽነት ይጠቀሙበታል (ሐመር ህዳር/ታህሳስ፡ 1994 14)። የጠበል ምንነትን በሚመለከት የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ሶስት ፍቺ ሰጥቶታል። አንደኛ፣ “ህመምተኞች ፈውስ ለማግኘት የሚጠጡት ወይም የሚጠቀሙበት የተለየ ውሃ”። ሁለተኛ፣ “በተፈጥሮ ፈዋሽነት ያለውና በታቦታት ሥም የሚጠራ የምንጭ ውሃ” እንዲሁም ለክርስትና ለተስካር፣ ለዝክር፣ ለማህበር የተዘጋጀ ድግስ” (2006፣ 580)።

[1] ይህን ይበል እንጂ የስነ ልሳን ሊቁ “ፀበል ግእዝ ሲሆን ጠበል ደግሞ አማርኛ ነው። ፀበል ከ”holy water” የተለየና ከመበስበስ ጋር የተገናኘ ትርጉም ያለው እንጂ የአማርኛውን ጠበል አይወክልም(ፕ/ሮ ባየህ ይማም ባህርዳር 14/08/2006 ሁለተኛው ዙር ሀገር አቀፍ የአማርኛ ቋንቋ አውደ ጥናት ላይ ባቀረቡት የጥናት ስራ ውስጥ ያነሱት ምሳሌ ነበር።

ተቀራራቢነት ያለው ሌላው ብያኔ "በእግዚአብሔር ሀይል ህሙማን የሚፈወሱበትና ልዩ ልዩ ተአምራት የሚደረግበት የተለየና የተቀደሰ ውሃ ነው(ፍኖተ ቅዱሳን፣ 1993፡ 96)። የውሃው ፈውስ በተፈጥሮ ሳይሆን በእግዚአብሔር ሃይል ነው በማለቱ ከመጀመሪያው ፍቺ ይለያል። ተቀራራቢነት ያለው ሌላው ብያኔ "እግዚአብሔር በአንዳንድ ቅዱሳንና ጻድቃን ላይ አድሮ ተአምራቱን የሚገልጽበት ቃል ኪዳን የገባበት ስለሆነ በጻድቁ ስም ተጠቅመው የታመሙት የሚፈወሱበት ውሃ ሁሉ ነው(መረሀ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት 1988፡ 103-104)።" ከላይ ባለው ብያኔ "በታቦታት ስም" የሚለውን በቅዱሳን ስም መባሉ የተሻለና ተገቢ[2] ይሆናል። ከሁለቱ የሚለየው "ለመድኃኒት የሚሆነው ውሃ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገባበት ሲሆን ለመዳን የፈለገም በባለጠበሉ ጻድቅ ወይም ቅዱስ ስም ተጠቅሞ ከህመሙ የሚድንበት ነው" ሲል ጠበሎቹ መጠሪያ ቅዱስ ወይም ጻድቅ እንዳላቸው ይጠቁማል።

የጠበል ምንጮች የሚገኙበትን ቦታ፣ መጠሪያቸውን እንዲሁም በመጽሀፍ ቅዱስ ስለጠበል የተጻፉትን በተመለከተ፣ "ጠበል(ሎች)፤ ጠቢል፡ ጠበለ)፤ በዱር፡ በገደል፡ በተራራ፡ የፈለቀ ውሃ፡ ክርስቲያን ሁሉ፣ በሥላሴ፡ በማርያም፡ በመላእክት፡ በጻድቃን፡ በሰማእታት፡ ስም፡ የሚጠመቅበት (ዮሐ ፪:፫:፬:፯።፱:፯)። ያቦ የጊዮርጊስ፡ ጠበል እንዲሉ(የሩፋኤል፡ ጠበል)በማለት ነው(ደስታ፣ 19 62፣ 535)።

ከዚህ በላይ ባየናቸው የጠበል ብያኔ መሠረት፣ ጠበል ከሚሰጠው አገልግሎት አኳያ በሶስት ይከፈላል። አንደኛው የረከሰን ለመቀደስ፣ ሁለተኛው ሀጥኡን ለማንጻት ሶስተኛው ህመምተኞችን ለመፈወስ የሚሉ ናቸው። ለዚህ ጥናት ተስማሚው ብያኔ፤ "ጠበል ማለት ህመምተኞችን ለመፈወስ የሚያገለግል ውሃ ነው" የሚለው ይሆናል። ምክንያቱም ለዚህ ጥናት የተመረጠው የጨፋ ጠበል ተገልጋዮች በሙሉ ወደ ጠበሉ የሚሄዱት ከሀጥያት ለመንጻት ወይም ለመቀደስ ብለው ሳይሆን ከህመም ለመዳን ሲሉ ነው።

የጥናቱ ትኩረት የሆነው የጎንዴ ጠበል በበላይነት የሚያስተዳድረው የሃይማኖት ተቋም የኢ.ኦ.ተ.ቤ ነው። ጠበል በፈለቀበት ወይም ባለበት አካባቢ በኢ.ኦ.ተ.ቤ.ሃይማኖት ደንብ መሠረት ቤተ-ክርስቲያን ይሰራል። አልፎ አልፎም ገዳም ይገደማል። ይህ ሲባል ግን የጠበሉ መፍለቅ ከቤተ-ክርስቲያኑ ግንባታ አይቀድምም። ምክንያቱም አንዳንዴ ቤተ-ክርስቲያን ባለበት ጠበል ይፈልቃል። አልያም በተለያየ መንገድ (በአብዛኛው በራእይ) "ውሃው ጠበል ነው፤ ከመለኮታዊ ሀይል ተገልጦልናል" በማለት ውሃ የነበረው ጠበል የሚሆንበት አጋጣሚ የተለመደ ነው። ሆኖም ማህበረሰቡ ከህመም ለመፈወስ የሚጠቀምባቸው የተለያዩ የተፈጥሮ ምንጮች ሁሉ ጠበል አይደሉም።

---

[2] ታቦት ወይም ቅዱስ የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ መሠረት አድርገን እነዚህን ሁለት ብያኔዎች ስንመለከት በታቦታት ስም ከማለት በቅዱሳን ስም መባሉ የተሻለ ነው። ምክንያቱም የሚቀድመው ቅዱሱ እንጂ ታቦቱ አይደለም። ታቦቱ በስሙ የሚቀረጽና የሚሰየም መከበሪያው ነው። ስለዚህ ጠበሎቹ በታቦታት ስም ሳይሆን በቅዱሳን ስም የሚሰየሙ ናቸው።

የጠበሉና የተፈጥሮ አዳኝ ፍል (ሙቅ) ውሃ[3] ተመሳስሏቸው ከህመም መፈወሳቸውና ለመፈወስ የሚሄዱ ሰዎች በሳይንሳዊ መንገድ ተጠንቶ የህክምና ባለሙያ አዞላቸው ሳይሆን "እድናለሁ" በሚል እምነትና ሲወራረስ በቆየ ትውፊት ለችግራቸው መፍትሄ ፍለጋ ብለው መጠቀማቸው ነው። ይህ ጥናት እነዚህ የተፈጥሮ ሙቅ(ፍል) ውሃን አይመለከትም።

ጥናቱ ትኩረት ያደረገበት የጠበል ስፍራ ኦሮሚያ ብሄራዊ ክልል አርሲ ዞን ሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ይገኛል። አርሲ ዞን የሚያዋስኑት በሰሜን ምስራቅ ሸዋ፣ በደቡብ ባሌ ዞን፣ በምእራብ ደግሞ ምእራብ አርሲ ናቸው። የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ከዐዲስ አበባ በስተ-ደቡብ በ222 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። ሌሙና ቢልቢሎ ወረዳን በምስራቅ እንቆሎና ሽርካ ወረዳ፣ በደቡብ የዋቤ ወንዝ፣ በስተ-ሰሜን ዲገሉና ጢጆ ወረዳ፣ በምእራብ ሙኔሳ ወረዳ ያዋስኑታል። የጨፋ/የጎንዴ[4] ጠበል "ጠበል ነው" ተብሎ የተባረከው በ1986ዓ.ም ሲሆን በኢ.ኦ.ተ.ቤ በአርሲ ሀገረ ስብከት ይተዳደራል።

የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት የጨፋ ጠበል ባለበት ወረዳ አጥኚዋ በሌላ ርእሰ ጉዳይ ጥናት ስታደርግ እግረ መንገዷን ለጠበሉ መገለጥ ምክንያት የሆነውን ራእይ ያዩት እማሆይ ሳህለማሪያምን ለማግኘት ችላለች። በዚህም መነሻነት የጎንዴን ጠበል በተመለከተ የተጠኑ ጥናቶች መኖር አለመኖራቸውን ዳሰሳ ስታደርግ የገዳሙን አመሠራረት በተመለከተ በ2000ዓ.ም አቶ ወርቁ ከተማ ካጠኑት በስተቀር ሌላ ጥናት አልተገኘም። የአቶ ወርቁ ጥናት የገዳሙን አመሠራረት መነሻ የሚመለከቱ ቃላዊ ትረካዎች ላይ እንጂ ጠበሉን የሚመለከት አይደለም። ስለዚህ የዚህ ጥናት አስፈላጊነት አንደኛ ይህን ክፍተት ለመሙላት ሲሆን ሁለተኛ የኢ.ኦ.ተ.ቤ አብያተ ክርስቲያናት ባሉበት በርካታ የጠበል ስፍራዎች ቢኖሩም በመጽሄት፣ በጋዜጣ እና በመሰል በራሪ ጽሁፎች ከተጻፈው ውጭ ጥናት አልተደረገባቸውም። ይህን ክፍተት ለመሙላት ጥናቱን ማጥናት አስፈላጊ ሆኗል።

የጥናቱ ዋና አላማ የጨፋ ጠበል ፎክሎራዊ ገጽታ ከተገልጋዮቹ አኳያ መግለጽና መተንተን ይሆናል። ዝርዝር አላማዎቹ፡-የጨፋ ጠበል ለጠበልነቱ መነሻ የሆነው ፎክሎራዊ ገጽታ መግለጽ። በጠበሉ የሚገለገሉት ስለጠበል ያላቸውን ልማዳዊ እምነት መለየት። እንዲሁም በጠበል የሚገለገሉ ግለሰቦች ጠበል በመጠመቅ የከዋኔ አጋጣሚ ልዩነቶቻቸው እንዳለ ሆኖ አንድ የሚሆኑባቸውን የከዋኔ አጋጣሚዎችን መተንተን ናቸው።

---

[3] ለዚህም ማሳያ የተፈጥሮ ፍል ውሃ ያሉባቸውን ቦታዎች መጥቀስ ይቻላል። ለምሳሌ ቦኩ ሚካኤል በኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ የሚገኘው አንዱ ሲሆን ሌላው በደቡብ ብሄር ብሄረሰብና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በሀላባ ልዩ ወረዳ የሚገኝ የአርቶ ፍል ውሃን ማንሳት ይቻላል። እነዚህንና ሌሎችም መሰል በተፈጥሮ አዳኝ ተብለው የታመመ ለመፈውስ የሚገለገልባቸው የተፈጥሮ ፍል ውሃ ያሉባቸው ቦታዎች ናቸው። እነዚህን በባለቤትነት የሚያስተዳድር የሃይማኖት ተቋም የለም። ከህመም ለመፈወስ በእነዚህ ውሃዎች ይነከራሉ።

[4].የአካባቢው ህዝብ ጎንዴ እና ጨፋ የሚሉትን ጠበሉ የሚገኝበትን አካባቢ መጠሪያ ስም አድርገው ይገለገሉበታል። ሁለቱንም ስሞች በተለዋዋጭነት ይጠቀሙበታል። ሆኖም በአስተዳደራዊ ስራ ላይ ጽሁፍ ላይ የሚያገለግለው ጨፋ የሚለው ስም ስለሆነ እኔም "የጨፋ ጠበል" በሚለው መጠሪያ ስም እጠቀማለሁ።

በጠበሉ ከሚገለገሉ ግለሰቦች ልምድና ተሞክሮ አኳያ ተጠቃሚዎቹ በሚያደርጉት ክዋኔና የጠበሉ ዳራ ትረካ ላይ ብቻ ያተኮረ ይሆናል፡፡ ከዚህ ውጭ ጠበሉን በበላይነት የሚያስተዳድረውን ገዳም አደረጃጀት፤ በጠበል ለሚገለገሉ ምእመናን ሃይማኖታዊ ደንብ እንዲሁም የጠበልን ሃይማኖታዊ ይዘት መመርመር የዚህ ጥናት የትኩረት ነጥቦች አይደሉም።

የጥናቱ ዓይነትና ዘዴ በፎክሎር ላይ የሚካሄድ ጥናት የሚያስፈልጉት የአይነት ወይም የትርጉም ባህርይ ያለው ነው። ዋንኛው የመረጃ ምንጭ ወጥ መረጃ በመስክ ጥናት ስምሪት አማካይነት ተጠኝው ህዝብ ባለበት በመገኘት በተለያየ የመስክ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ የተገኘ ነው። መረጃውን ለማሰባሰብ አጥኚዋ በቦታው በመገኘት በምልከታ እና በቃለ-መጠይቅ ዘዴ በመጠቀም መረጃው በድምጽ በምስል እና በጽሁፍ ተሰብስቧል። የአንዱን ዘዴ ድክመት በሌላው ጥንካሬ በማካካስ ለምሳሌ በምልከታ የተገኘው መረጃ ተጨማሪ ምላሽ ሲፈልግ ቃለመጠይቅ በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል። ሁለተኛው ከቤተ-መጻህፍት፣ ከቤተ-መዛግብት፣ ከሳይንሳዊ ጆርናሎች፣ ከኢንተርኔት፣ ወዘተ፣ የቀረቡ የጽሁፍ መረጃዎች ለማሰባሰብ የሚያስችል ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ ነው (Kothari 2004; Fenngan 1992)። ለዚህ ጥናት የጽሁፍ መረጃዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል። የመረጃ ትንተናው ከመስክ እና ከሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎችን በመግለጽ፣ በመተንተንና በመተርጎም በገለፃ፣ በትረካና በትርጉም ስልቶች ቀርበዋል፡፡

## 2 .የጽንሰ ሀሳብ መነሻ

የጽንሰ ሀሳብ መነሻ ፎክሎር ሲሆን የፎክሎር ጥናት በአውድ መረጃን መሰብሰብ አስፈላጊ ነው። ከመስክ ለተገኙ መረጃዎችም መነሻ ጽንሰ ሀሳቦችን በተለይ ከዚህ ጥናት ርእሰ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ጥቂት ማለት አስፈለጊ ስለሆነ ፎክሎር እንዲሁም ከሚያጠናቸው ዘርፎች አንዱ ስለ ሆነው ሚት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 2. 1 ፎክሎር

ፎክሎር "ፎክ" እና "ሎር" በሚሉ ቁልፍ ፅንሰ-ሀሳቦች ፍቺዎች አማካይነት የሚገለጽ ሲሆን "ፎክ" ማለት ቢያንስ አንድ የጋራ ማስተሳሰሪያ ባሕርይ፣ ለምሳሌ፡- ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ሙያ፣ ወዘተ፣ ያላቸው ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ስብስብ ማለት ነው። ፎክ የሚባለው ለምሳሌ፡- የቤተሰብ አባላት፣ ማህበራዊ ቡድኖች፣ ጎሣዎች፣ ብሔረሰቦች፣ ከዚያም አልፎ ሀገሮች፣ ወዘተ፣ የሚያካትት ቃል ነው። Dundes "ሎር" ማለት ፅንሰ-ሀሳብ በአጠቃላይ "ዕውቀት" የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡ ይህም አንድ ማህበራዊ ቡድን ወይም ቡድኖች በመካከላቸው የሚያስተሳስራቸው የወል "እውቀት" ማለትም፡-ርዕዮተ-ዓለም፣ ስለ ዓለም ያለው አመለካከት፣ ጥበብ፣ ዘዴ (የኑሮ፣ የችግር አፈታት ዘዴ፣ ወዘተ)፣ እምነት፣ እሴቶች፣ ደንብ፣ ሕግ፣ የሕይወት መመሪያ፣ ወዘተ፣ ሁሉ የሚያካትት ሠፊ ፅንሰ-ሀሳብ ነው(Dundes 1965: 1-4; 1980:54-60)። ይህ ማለት ሀሳቦች፣ ደንቦች፣ የዕለት ተዕለት የሕይወት፣ የግልና የማህበረሰብ ባሕርያትና ድርጊቶች መመሪያዎችን፣ ጨምሮ የሚይዝ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ሃይማኖትና እምነት በራሱ አንድ የጥናት መስክ ቢሆንም በፎክሎር ጥናት በተለይም በሚቶሎጂ መስክ ከሚጠኑት አንዱና ዐቢይ ጉዳይ ነው፡፡ የፎክሎር አንዱ አብይ ዘርፍ በሆነው በሀገረ-ሰባዊ ልማድና በሃይማኖት መካከል ቁርኝት አለ (Larry 1986, in Fekade 2003:53)። ከፎክሎር የጥናት ዘርፎች በተለይ እምነት ነክ ሀሳቦች ከሚት ጋር ይገናኛሉ። ሚት የሚባለው አንድ ፍጥረት እንዴት እንደተፈጠረ ማብራሪያ የሚሰጥ ነው። ለምሳሌ አንድ በዓለም ያለ ነገር እንዴት ወደ ዓለም መጣ? ለሚለው ምላሽ የሚሰጥና ስለ ፍጥረት የሚያትተው ገለጻ ሲሆን ሀተታው ያለው በሰው ልጅ የእውቀት እድገት ለውጥ ውስጥ ነው። ሊገለጹ የማይችሉ ክስተቶች በፈጣሪ ቀጥታ ጣልቃ ገብነት ውስጥ ይፈረጃሉ(Joseph Campbell, 1968)።

ሌላው ስለሚት ብያኔ የሰጠው የዘርፉ ባለሙያ "ሚት እንደ ትረካ ቢበየን እላለሁ፤ ምንም ይሁን ምን ትረካ ምክንያታዊ ይመስላል። ትረካው ስለ ምን ያወራል? ካልን ሚት እንደ ትረካ ተደርጎ ይወሰዳል። ከሁሉም በላይ ሚት ለፎክሎሪስቶች ስለ አለም አፈጣጠር የሚያትት ነው። በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለቱ[5] የዘፍጥረት ታሪኮች ስለሚት የሚያረጋግጡ ምእራፎች ናቸው"(Robert A.Segal 2004, 5)።

የተለያዩ የሚት አይነቶች አሉ። አንዱ የስነ ህላዌ ሚት (Cosmogony Myth) ሲሆን በአብዛኛው የሚይዘው አለም፣ የሰው ልጅ ከተፈጠሩ በኋላ የተፈጠሩ በሰው መካከል የሚፈጠሩ አስደናቂ ሥረዓቶች(ባህሎች) የሚፈጥር ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ ከፈጠረ በኋላ አዳምን ፈጠረ። አዳምም ለፍጥረታት ሁሉ ስም ስጥ ተባለ፤ እግዚአብሔር የፈጠራቸው ደግሞ መፍጠር ሲጀምሩ ሚት ነው። በአጠቃላይ ሚት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚነገሩ ትረካዎች ሲሆኑ እንደ እውነት ስብስቦች የሚቆጠሩ በአንድ ባለፈ ጊዜ የተከሰተ ክስተት ነው። በአንድ ሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ትረካዎች ለሚያምንበት ማህበረሰብ የተቀደሰ ትረካ ሲሆን ለማያምንበት ደግሞ እንደማንኛውም ትረካ ሊታሰብ የሚችል ነው።

በእነዚህ መሠረታዊ ግንዛቤዎች መነሻነት የጨፋን ጠበል ፎክሎራዊ ገጽታ እንመለከታለን። መጀመሪያ ጠበሉ ጠበል ከመሆኑ በፊት እንደማንኛውም የምንጭ ውሃ አገልገሎት ይሰጥ ነበረ። ከ19 86ዓ.ም ጀምሮ "ጠበል ነው" የሚለው ራእይ ላይ የተመሠረተ ትረካ ነው። ትረካውን መሠረት አድርጎ እምነቱ ከሀያ አመት በላይ ከአንዱ ወደሌላው መረጃው በቃል እየተላለፈ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። ይህን ሂደት ጥናቱ እስኪጠናቀቅ ያለውን ከፎክሎራዊ ይዘቱ አኳያ እንደሚከተለው ቀርቡዋል።

[5] ምእራፍ አንድ እና ሁለት፣ ስለኤደን ገነት ታሪክ(ዘፍጥረት3)ስለኖህ ታሪክ(ዘፍጥረት 6-9)

## 3.የጨፋ ጠበል ፎክሎራዊ ገጽታ

### 3.1 የጨፋ ጠበል ዳራ

በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ የተለያዩ የጠበል ቦታዎች[6] አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው የጨፋ ጠበል ሲሆን ለገዳም መገደም ምክንያት የሆነ የጠበል ስፍራ ነው። በጨፋ አካባቢ የነበሩ ነዋሪዎች ለጠበል መነሻ የሆነውን የአስታጥቄ ምንጭ ውሃ ለተለያየ ግልጋሎት ያውሉት ነበር። “ምንጯ አስታጥቄ በሚባል ሰው መሬት ላይ በመፍለቋ ስያሜዋ የአስታጥቄ ምንጭ ለመባል በቃች። የአስታጥቄ ምንጭ በአርሲ ዞን በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ በጨፋ ቀበሌ ውስጥ የምትኝ እና ቀደም ሲል ለመጠጥ ግልጋሎት ለልብስና ለገላ መታጠቢያነት ታገለግል የነበረች ምንጭ ናት (ወርቁ 2000፡ 44)”።

እማሆይ ሳህለማሪያም[7] የአስታጥቄ ምንጭ ተብሎ የሚታወቀውን ውሃ እንዲባረክ እስካደረጉበት ግንቦት 12/1986 ዓ.ም ድረስ ጠበል መሆኑ አይታወቅም ነበር። የአስታጥቄ ምንጭ ቀደም ሲልም ገዳም እንደነበረና በ16ኛው መ/ክ/ዘ በእስልምና ሃይማኖት ተከታዩ *አህመድ ኢብን* ኢብራሂም አልጋዚ (አህመድ ግራኝ ) የወደመ የአንድነት ገዳም እንደነበረ እማሆይ ሳህለማሪያም በትረካው ውስጥ ገልጸዋል። በአንድነት ገዳም ውስጥ ወድመዋል የሚባሉትንም ሲዘረዝሩ፡- በሴቶቹ ገዳም፣ የቁስቋም ቤተ-ክርስቲያን፤ በወንዶች ገዳም የአቡዬ ገብረመንፈስ ቅዱስና የመስቀለ ኢየሱስ ቤተ-ክርስቲያን እንደነበረ። አወዳደማቸውም የመስቀለ ኢየሱስ ቤተ-ክርስቲያን በ*አህመድ ኢብን* ኢብራሂም አልጋዚ እንደተቃጠለ፣ የአቡዬ ገብረመንፈስ ቅዱስ ቤተ-ክርስቲያን እንደተሰወረ ይገልጻሉ። በተጨማሪም በተለያየ ጊዜ ንዋየ ቅድሳት፣ የሰው አጽሞች[8] እንዲሁም ምልክት ያለባቸው ተክል ድንጋዮች ተገኝተዋል።

---

[6] ለምሳሌ “ጭባ ሚካኤል” በሚገኝበት ቀበሌ ስም፣ “አዋሬ ገብርኤል” በቀበሌውና በቤተክርስቲያኑ ስም፣ “አቦ ጠበል” በቤተ-ክርስቲያኑ ስም፣ “ጋራ እግዚአብሔር አብ ጠበል” በቦታው አቀማመጥና በቤተክርስቲያኑ ስም ይጠራሉ።

[7] እማሆይ ሳህለማሪያም በዓለም ስማቸው እመት የሺ ሀረግ ይባሉ ነበር። በቀድሞ አጠራሩ ጎንደር ግዛት ጋይንት ወረዳ ልዩ ስሙ ጨጨሆ መድህኒዓለም በ1943ዓ.ም ተወለዱ። የመጀመሪያ ልጃቸውን ከወለዱበት ቀን ጀምሮ የእግዚአብሔር መልእክት በራእይም በቀንም እየተገለጠ ለሌሎች ድህነት የሚሆን መልእክት ወደ ዓለም እንዲያደርሱ ይነገራቸው ነበር። መልእክት ሲደርሳቸው ለማንም ሳይነግሩ ብቻቸውን ይጨነቁ ነበር። ከመልእክት አንዱ ወደ ደቡብ የሀገራችን ክፍል እንደሚሄዱና በዚያም በእሳቸው አሳሳቢነት ብዙ ድህነት እንደሚደረግ ነበር። ወደ አርሲ ክፍለ ሀገር ሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ባለቤታቸው፣ ልጆቻቸውና በከፊል ዘመዶቻቸው ጭምር በተለያየ ጊዜ መጥተው ኑሯቸውን አሁን የጨፋ ጠበል በሚገኝበት የገጠር ቀበሌ አደረጉ። እመት የሺሀረግ እንዲመነኩሱ በተደጋጋሚ ከፈጣሪ መልእክት ይነገራቸው ስለነበር፣ ትዳራቸውን ትተው በ986ዓ.ም መነኑ። በኢ.ኦ.ተ.ቤ. ሥረዓትና ደንብ መሠረት ጥቅምት 6/1987 ዓ.ም መነኮሱ። የዓለም ስማቸው እመት የሺ ሀረግ አለሙ ቀርቶ፤ እማሆይ ሳህለማርያም ሆነ። በዚያው ምናኔ በገቡበት ቦታም መኖራቸውን ቀጠሉ። እማሆይ ሳህለማርያም ከጠበሉ ሌላ ስለ ቦታው የተገለጠላቸውን ምስክርነቶች ይሰጡ ነበር። ይህንን መረጃ ከ2004 እስከ ግንቦት1 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ በተለያየ ጊዜ ለአጥኚዋ ከነገሯት መካከል የተወሰደ ነው። የጨፋ ጠበል እዚህ እንዲደርስ በየጊዜው ለሚመለከተው አካል የታያቸውን ራእይ በመናገር እንዲሁም ማሳየት በምንኩስናና በብህትውና ህይወት በዚያው በጠበሉ ስፍራ ይኖሩ ነበር። በ64 አመታቸው ሰኔ16/2006 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየት ለ21 አመት በኖሩበት የጠበሉ ስፍራ የጸሎት ቤታቸው ውስጥ አጽማቸው አርፏል።

[8] የተገኙት አጽሞች በ*አህመድ ኢብን* ኢብራሂም አልጋዚ ጦር የተገደሉ መነኮሳትና የገዳሙ አገልጋዮች አጽም ነው(ቃለ-መጠይቅ እማሆይ ሳህለማሪያም ሀምሌ 26፣ 2005)።

ጠበሉ ከፈለቀ በኋላ እማሆይ ሳህለማሪያም በራእይ እየታያቸው፣ ቀደም ሲል የአንድነት ገዳም ነበር የሚለውን ቃላዊ ትረካ ተከትሎ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል። ከተሰሩት መካከል ለምሳሌ ተቃጥሏል በተባለው መስቀለ ኢየሱስ ቤተ-ክርስቲያን እና ተሰውሯል በተባለው የአቡዬ ገብረመንፈስ ቅዱስ ቤተ-ክርስቲያን ምትክ የመድሀኒዓለም ቤተ-ክርስቲያን ተሰርቶ ጥቅምት 27/1987 ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ ተከብሮ አገልሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። የሴቶች ገዳም ውስጥ ነበረ የተባለው የቁስቋም[9] ቤተ-ክርስቲያን ህንጻው ተሰርቶ በ2002ዓ.ም ህዳር 6 ታቦቱ ገብቶ አገልግሎት ይሰጥበታል። በመጋቢት ወር 1998 ዓ.ም በብጹ አቡነ ናትናኤል የቀድሞው የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ "የጨፋ መድሀኒዓለም፣ ደብረ ቁስቋም ቅድስት ማርያምና ቅድስት ሰሎሜ የሴቶች አንድነት ገዳም" በኋላም በ2002 ተሻሽሎ "የጨፋ መድሀኒዓለም ደብረቁስቋም፣ ቅድስት ማርያም ወሰሎሜ አንድነት ገዳም" በመባል የአንድነት ገዳም ሆኖ በዚሁ መጠሪያና ደንብ ይተዳደራል። ይህ ጥናት እስኪጠናቀቅ(ሰኔ 2009) 17 ሴት መነኮሳት እና 15 ወንድ መነኮሳት በገዳሙ ይኖራሉ።

ውሃው ወደ ጠበልነት መቀየር፣ ለአብያተ ክርስቲያኑ መታነጽ፣ በገዳም ደንብ በመተዳደር አስራ ሰባት ያህል መነኮሳት የሚኖሩበት ገዳም እንዲገደም ምክንያቱ የእማሆይ ሳህለማሪያም ራእይ ነው። ራእዩን ይመለከተዋል ላሉት የኢ.ኦ.ተ.ቤ አካል ይተርካሉ። የሚመለከተው አካል በተነገረው ትረካ መሠረት ከአካባቢው ህዝብ ጋር በመስራት አሁን ላለበት ደረጃ በቅቷል። ሆኖም ትረካውን ለዚህ ጥናት ከእማሆይ ሳህለማሪያም በቃል መስማት እንጂ በጽሁፍ የሰፈረ አይደለም። የጠበሉ ተገልጋዮችም ይህንኑ ትረካ በቃል ይቀባበሉታል። የቃል ትረካው መሠረት ያደረገው ጠበል አሁን ያለበት ሁኔታ እና ተገልጋዮቹን በሚመለከት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 3.2 በጠበሉ እነማን ይገለገላሉ ምንስ ይሉታል?

አጥኚዋ መረጃ ለማሰባሰብ ወደ ሥፍራው በተገኘችበት ወቅት የተመለከተቻቸው ጠበልተኞች ከጾታ አንጻር ሁለቱም ሲሆኑ ከእድሜ አኳያ በእቅፍ ካሉ ህጻናት ጀምሮ በሌሎች ድጋፍ እስከሚመጡ አረጋዊያን ድረስ ይገኙበታል። ተጠማቂዎቹ የእስልምናና የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው።

ጠበል ፈጣሪ ከሌሎች የውሃ ምንጮች በተለየ ለመድሀኒትነት መምረጡን፣ ለመረጣቸው ሰዎች መግለጡ ጠበል ያሰኘዋል። ሰዎችም ከተለያየ በሽታ ያድናል ብለው በማመን ይጠቀሙበታል። የተለየ አክብሮት በመስጠትም ጥበቃ ያደርጉለታል። ስለጠበል ምንነት የሃይማኖት መጻህፍት እና መዝገበ ቃላት ብቻ ሳይሆኑ ተገልጋዮቹ የተጻፉትን ሳያነቡ ከራሳቸው ልምድ ተነስተው ብያኔ ይሰጣሉ። ለምሳሌ የጥናቱ ቦታ ላይ የነበሩ በጠበሉ በተደጋጋሚ ተነክረው የፈለጉትን ያገኙ ግለሰብ የሰጡት የጠበል ብያኔ የሚከተለው ነው።

[9] የሴቶች ገዳም ውስጥ የነበረው የቁስቋም ቤተ-ክርስቲያን ምትክ የኪዳነምህረት ቤተ-ክርስቲያን እንዲሰራ መታዘዛቸውን ተናግረው ነበር። ሆኖም አሁን የተሰራው የቁስቋም ቤተ-ክርስቲያን ሲሆን ህንጻው ተሰርቶ በ2002ዓ.ም ህዳር 6 ታቦቱ ገብቶ አገልግሎት ይሰጥበታል።

ጠበል ለህመም መፈወሻነት ይውል ዘንድ ፈጣሪ ከውሃ ምንጮች የመረጠው ቅዱስ ውሃ ነው፡፡ 'ከሰው መርጦ ለሹመት፤' ከእንጨት መርጦ ለታቦት ይባል የለ፡፡ ጠበል የሚሆን ውሃም እንዲሁ ነው። ፈጣሪ አንዱን የውሃ ምንጭ ኅርፍ አድርጎ ሀገር ያጠፋበታል፡፡ አንዱን ደግሞ ጠበል አድርጎ እውሩን ያበራል። የታመመን ሲፈልግም ሞተ የተባለውን ያድናል፡፡ [10] በማለት ለመድሀኒትነት ፈጣሪ ለሰው ልጅ እንደፈጠረው እንዲሁም ሰዎች በምን መልኩ እንደሚጠቀሙበት ያስረዳሉ።

በሀገራችን አውድ ውስጥ ሲታይ በጠበሉ መጠቀም ለፈለገ ለየትኛውም ሃይማኖት ተከታይ አይከለከልም፡፡ ለምሳሌ በወሎ ጥናት ያደረጉት "ጠበል መጠመቅ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም ነው (Kalkelachew, 1997፣ 74) ሲሉ ይጠቁማሉ። በመሆኑም በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ የጠበል ምንጮች የሚገለገሉት የእስልምና እና የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። አንድ ሰው ከተፈወሰ ለባለ ጠበሉ ቅዱስ (ቅድስት)የተሳለው ስዕለት ካለ ለማድረስ ወይም ለማመስገን ወደ ቤተ–ክርስቲያን ይሄዳል። በመሄዱ ለምን ወደ እኔ የአምልኮ ስፍራ መጣህ የሚለው የለም፡፡ ይህን ጥያቄ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ምእመናን እንዳያነሱ ያስተማራቸው ወይም የሚያስገድዳቸው ሃይማኖታዊ መሠረታቸው ሳይሆን በአብሮ መኖር ውስጥ ያዳበሩት ደንብ ነው፡፡

### 3.3 ጠበሉ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?

በጨፋ(ጎንዴ) ጠበል በአርባ አራቱ ቅዱሳን ስም[11] የተሰየመ አርባ አራት ምንጮች አሉት፡፡ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ በመመስረት ጠበሉን በአራት ከፍሎ ማየት ይቻላል። አንደኛው ክፍል የምንጩን ስር ቆፍሮ ተጠማቂው ቆሞ ወይም ተቀምጦ ለመነከር እንዲሁም ለመቅዳት አመቺ ሆኖ የተበጀ ነው። በዚህ በአንደኛው ክፍል የምናያቸው በአስራ ሁለቱ ቅዱሳን ስም የተሰየሙ ምንጮች ለመውረድ አመቺ እንዲሆኑ በአራት ሀያ፣ ሀያ ሳንቲ ሜትር ስፋት ባላቸው አሸንዳዎች ውስጥ አልፈው ይወርዳሉ። የዚህ ዓይነቱ ጠበል መጠመቂያ ከሁለት ቦታ ላይ ይገኛል። ለተጠማቂዎች ምቹ እንዲሆንም ዙሪያው በእንጨትና በጨርቅ ጣራው በቆርቆሮ ተሸፍኗል። የአንዱ ከለላ ስፋት ስምንት ካሬ ሲሆን የሁለተኛው አስር ካሬ ነው። ለመጠመቅ ምቹ የሆኑት ጠበሎች በእነዚህ ሁለት ከለላ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ከምንጩ የሚወርደው የጠበል

---

[10]መረጃ ሰጭ:- አቶ ከበደ ሆሮሶ፣ እድሜ 56፣ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ፣ በግብርና ስራ የሚተዳደሩ(ቃለ-መጠይቅ ጨፋ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ጥር 21/2007)፡፡

[11] አርባ አራቱ ቅዱሳን 1.አቡዬ ገብረ መንፈስ ቅዱስ 2.ቅዱስሚካኤል 3.አቡነ ዘርአ ብሩክ 4.መጥምቁ ዮሀንስ 5.ቁስቋም 6.ገብረክርስቶስ 7.ኪሩቤል ሱራፌል 8.ገላውዲዮስ 9.አቡነአረጋዊ 10.ገብርኤል11.ኪዳነ-ምህረት 12.በአለ-ወልድ 13.ሩፋኤል 14.አማኑኤል 15.መድሀኒዓለም 16.ድርሳነ ሰንበት 17.ተክለሀይማኖት 18.ሳሙኤል 19.ክርስቶስ ሰምራ 20.አርሴማ 21.ማርያም 22.ዮሴፍ 23.ሰማእቱ ጊዮርጊስ 24.ስላሴዎች 25.እስጢፋኖስ 26.ራጉኤል 27.ርህወሰማይ 28.ዮርዳኖስ 29.ባህታማርያም 30.ፋሲለደስ 31.እያቄም ወሀና 32.አቡነኪሮስ 33.ልደተስምኦን 34.እግዚአብሔርአብ 35.አቡነሀራ 36.ወልደአልፋ 37.የአብቃል 38.ባዛንቃማርያም 39.ልደታማርያም 40.ያሬድ 41.ኡራኤል 42.ወልደነጎድጓድ 43. አርባአራቱ 44.ብሩክ ናቸው(ቃለ-መጠይቅ እማሆይ ሳህለማሪያም ሀምሌ 23 2005)፡፡

መጠን ከሌሎቹ ጠበሎች በላይ ሲሆን ከአንዱ አሸንዳ ብቻ በደቂቃ ከአስር ሊትር በላይ ጠበል ይወርዳል። ተጠማቂዎች በዚህ አሸንዳ ስር በመቀመጥ ጠበሉን በሙሉ አካላቸው ላይ እንዲፈስ በማድረግ ይነከራሉ። ተጠማቂ ኖረም አልኖረ ጠበሉ ሲፈስ ውሎ ያድራል።

ሁለተኛውን የጠበል ክፍል የሚያመነጩት ምንጮች አሁን በሚገኙበት ሁኔታ አብዛኞቹ ለመጠመቅም ሆነ ለመቅዳት የማያመቹ ናቸው። ጠበሉን ለመቅዳት ለዚህ አገልግሎት ብለው የታዘዘውን ጾም የጾሙና የተፈቀደላቸው አገልጋዮች ብቻ ናቸው። ለመቅዳትም ሆነ ለመጠመቅ ምቹ ያልሆኑት በአብዛኛው በተለያዩ ቅዱሳን ስም ከተሰየመው መካከል "ይህኛው እንዲቀዳልኝ እፈልጋለሁ" ብሎ ለጠየቀ ሰው ብቻ በመቅዳት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ናቸው።

ሶስተኛው ክፍል አርባ አራቱ ጠበል በመባል ይጠራል። አርባ አራቱ የተባለበት ምክንያት አርባ አራቱ ምንጮች (ሁሉም የጠበል ምንጮች) በአንድነት የሚገናኙበት እና የተዋሀዱበት ስለሆነ ነው። አርባ አራቱ በተባለው ጠበል የአጠማመቁ ክዋኔ ከሌላው ለየት ያለ ሲሆን ተጠማቂዎች በወራጁ ጠበል ውስጥ ገብተው የሚነከሩበት ነው። በአንደኛው ክፍል ላይ በሚገኘው ጠበል ለመነከር በቅድሚያ አርባ አራቱ ጠበል መነከር ግዴታ ነው። አርባ አራቱ ጠበል ብቻ ተጠምቆ አንደኛው ክፍል ላይ የተገለጸውን ጠበል አለመነከር ይቻላል። እነዚህ በሶስት ክፍለን የተመለከት ናቸው ጠበሎች በጠበሉ ቅጽር ግቢ በተከለለው ቦታ ውስጥ የሚገኙ ናቸው።

አራተኛው ቡሩክ ይባላል። ቡሩክ የሚባለው አርባ አራቱ ጠበል የተወሰነ ርቀት ሄዶ ከታጠረው አጥር ውጭ፣ የገዳሙን ክልል አቋርጦ ከሚያልፈው አነስተኛ መጠን ካለው ወንዝ ጋር ተቀላቅሎ የሚወርድ ጠበል ነው። ከጠበሉ ግቢ ቢወጣም በገዳሙ ክልል ውስጥ ይገኛል። እማሆይ ሳህለማርያም ስለ አራተኛው የጠበል ክፍል እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> በ2004 ዓ.ም የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑች አንዲት ወጣት ታማ ራቅ ካለ ቦታ ቤተሰቧ ይዟት ይመጣል። አንድ ቀን እንደ ተጠመቀች የወር ልማዷ ስለመጣ እስከምትነጻ ወደ መጡበት ይዘዋት ተመለሱ። ከነጻች በኋላ ተመልሰው መጥተው ጠበሉን ሊነከሯት ሲጠጉ ያለ ቀኑ በድጋሚ የወር ልማዷ ይመጣና ሳትጠመቅ ትቀራለች። ለመጠመቅ ስትል በተደጋጋሚ ሳንካ ሆኖባት እሷም በህመም፤ ቤተሰቧ በመመላለስ ደከሙ። ድካማቸው የልጅቷ ስቃይ አንጀቴን አላወሰው። አልቅሼ መድዬን[መድሀኒዓለም] ለመንኩ።… በኋላ ይህን ከአርባ አራቱ ጠበል በታች ያለውን ከወንዙ ውሃ ተቀላቅሎ የሚሄደውን ጠበል 'ስሙን ቡሩክ በይው እህል የበላም፤ ያልነጻም መጥቶ ይጠመቅበት ይድናል' አለኝ።[12]

ቡሩክ የሚለውን ስያሜ ለጠበሉ ለመስጠት ምክንያት የሆነችው ህመምተኛም በዚሁ ጠበል

[12] የመረጃ ምንጭ፡- እማሆይ ሳህለማርያም፣ እድሜ 64 (ቃለ-መጠይቅ ሚያዝያ 22/2006 ዓ.ም)።

ተጠምቃ ከህመሟ ድና ወደ ሀገሯ እንደተመለሰች ገልጸዋል። ከ2004 ዓ.ም በኋላ ይህ ስፍራ በሌላው የጠበሉ ክፍል ለመጠመቅ የሚገባውን ያልፈጸሙ ሁሉ የሚጠመቁበት የጠበል ስፍራ ሆኖ ያገለግላል።

### 3.4 በጠበሉ እነማን እንዴትና መቼ ይጠቀሙበታል?

በጨፋ ጠበል በየእለቱ ህሙማን ከህመማቸው ለመዳን ሲሉ ጠበል ይነከራሉ። ጠበሉን ይጠጣሉ። በጠበሉ ለመነከር የሃይማኖት፣ የጾታ እንዲሁም የእድሜና ሌላም መሰል መስፈርት አይጠይቅም። ቢሆንም እስከ አሁን የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች ወደዚህ ጠበል ስፍራ እንዳልመጡ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ። እንዲያውም የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች ወደጠበል የሚሄደውን ጠበልተኛ እንደሚቃወሙ እንደሚከተለው ገልጸዋል።

> ወደ ጠበል የሚመጡትን በመንገድ ላይ እያስቆሙ 'ይህ እኮ ውሃ ነው አያድናችሁም! የሚያድናችሁ ኢየሱስ ነው። ጌታን ተቀበሉ 'እያሉ እንደሚያስቸግሯቸው የሚመጡ ጠበልተኞች ይነግሩናል። እንዲሁም አንድ ጊዜ እኔ እዚሁ ጠበሉ ግቢ ውስጥ ሆኜ እዚህ አካባቢ ያሉ ጴንጤዎች [ፕሮቴስታንቶች] 'ውሃው ምንም ሃይል እንደሌለው ገብተን እናሳያችሁ' በማለት መጡ። አንደኛው ቀድሞ ገባ። እኔም ከጠበሉ በላይ ካለው ጫካ ሆኜ አየዋለሁ። (ከዚያ በፊት አንዴም እንዲሁ ሰው በሌለበት መጥቶ ሊመታኝ ቃጥቶት የነበረ ሰው ነው፣ ደግሞ የመጣው።) ይህም ሰው ከጓደኞቹ ቀድሞ ወደ ጠበሉ የመጀመሪያው ክፍል ለመግባት መንገድ እንደ ጀመረ ሜዳው ላይ ወደቀ። በወደቀበት ሆኖ ማንም ሳይጠይቀው ለምን እንደ መጣ መሬት ላይ እየተንፈራፈረ ለፈለፈ። አብረውት መጥተው ከውጭ የቀሩት የእሱን መጮህ ሲሰሙ በሩጫ ከአካባቢው ጠፉ። ከዚያ በኋላ በመንገድ ላይ ሆነው ጠበልተኞች እንዳይመጡ ማከላከል እንጂ ደፍረው ወደዚህ ጠበል ግቢ የገቡ አልገጠመኝም።...[13]

የእስልምና እና የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች በመተሳሰብና በመናበብ አንዱ ለሌላው እያገዘና እየተረዳዳ በዚህ የጠበል ስፍራ ይገለገላሉ። በአንጻሩ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች አይገለገሉም፡፡ ጠበሉ በሚገኝበት ገዳም ስር በሚተዳደረው መድህኒዓለም ቤተ-ክርስቲያን ካነጋገርኩዋቸው መረጃ ሰጭዎች መካከል የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑት ወ/ሮ አሚና እንዲህ ይላሉ፡፡

> የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ነኝ። የመጣሁት ስዕለቴን ላስገባ ነው። የተሳልኩት ልጄ ዩንቨርሲቲ ገብቶ አራት አመት በሰላም ሲማር ቆይቶ ወደ አምስተኛው ሊደርስ ሲል ታመመ። በጠና ታሞ በሰንሰለት አስረው አመጡልኝ። እኔም ከዚያ በፊት ሴት ልጄ እብድ ውሻ ነክሷት ታማ

[13] መረጃ ሰጭ፤ እማሆይ ሳህለማርያም፣ እድሜ 63(ቃለ-መጠይቅ ሀምሌ 11 ቀን/ 2005 ዓ.ም)።

> በእግዚአብሔር አብ ጠበል ድናልኝ ስለነበር ይህን ልጅም ወደ ጎንዴ ጠበል ይዤው ሄድኩ። ስሄድ ቀኑ16 ስለ ነበረ ጎረቤቴ ለኪዳነምህረት ስለት ግቢ ስትለኝ፣ ገባሁ። ልጄንም ከዚያ ቀን ጀምሬ ለ14 ቀን እዚያው ቁጭ ብዬ አስጠመኩት። እሱም ዳነልኝ።[14]

የእስልምናና የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች ጠበል መነከርን በጋራ የእኔ የሚሉት የሚጠቀሙበት አብሮ በመኖር ሂደት በውስጣቸው ያሰረፁትና የሚጋሩት ክዋኔ ነው፡፡ ይህንም በተመለከተ በጠበሉ ከሚገለገሉት መካከል አንደኛው ሲገልጹ "አላህ መድህኒት ሁን ብሎ ለእኛም ከደጃችን ላይ ያመጣው መድህኒት ነው፡፡ አያቶቻችን ለከብት መዋያ እንጂ መች እንዲህ ዓይነት መድህኒት አገኙ፡፡ ጠበልነቱን ያወቅነው እኮ አሁን ነው። በእኔ ልጆች እድሜ፡፡"[15] በማለት ይገልፃሉ፡፡

ወደ ጠበል የሚመጡ ሰዎች የህመም ዓይነቶች የተለያዩ ናቸው። በተደጋጋሚ ተጠማቂዎች ከሚያነሷቸው የህመም ዓይነቶች መካከል ለምሳሌ በእርኩስ መንፈስ መያዝ(ቡዳ፣እጅ-ሰብ፣ ልክፍት)፣ ሰውነት አልታዘዝ ማለት በተለይ እጅ እግርና ወገብ (ይህንንም ብርድ በሽታ ይሉታል)፣ የራስ ምታት፣በቆዳ ላይ የሚከሰቱ የተለያየ መልክ ያለው በሽታ፣ የአይንና የሆድ ህመም በተለይም ሌላው ሳያውቁ "መድኃኒት አጠጥቶናል" የሚሉ ጠበሉን በብዛት ይጠጣሉ፡፡ የህመም አይነቶችን በጠበል የሚድኑ እና በህክምና የሚድኑ ብለው ይመድቧቸዋል። በተለይ ከላይ የተዘረዘሩት "በጠበል ይድናሉ" የሚባሉ የህመም አይነቶችን ለይተው ይዘረዝሩዋቸዋል። እንደገና ጠበሉን በመጠመቅ ብቻ የሚድኑ እንዲሁም ጠበሉን በመጠጣት እና በመጠመቅ እንዲሁም በመጠጣት ብቻ የሚዳኑ የህመም አይነቶች ብለው ምድብ ይሰጧቸዋል። በተለይ ለሆድ ውስጥ ህመም ጠበሉን በብዛት መጠጣት ፍቱን እንደሆነ ይታመናል።

### 3.5 የጠበል አጠማመቅ ክዋኔ

ከዚህ ቀጥለን የጠበል አጠቃቀምን (ክዋኔን) በአጭሩ እናያለን፡፡ አጥማቂው ማን ነው? ተጠማቂዎችስ እነማን ናቸው? መቼና የት፣ እንዴት፣ በማን ይጠመቃሉ? በሚሉት ጥያቄዎች ላይ እናተኩራለን፡፡ ተጠማቂዎችን ስንመለከት የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችን የሚያጠቃልል ሆኖ እናገኛለን፡፡ ጠማቂዎቹ በደንቡ መሠረት በምንኩስና ህይወት የሚኖሩ አገልጋዮች ብቻ ወደ ጠበሉ መጠመቂያ ሥፍራ ይገባሉ። ሆኖም የጨፋን ጠበል ከሌሎች የጠበል ስፍራ ልዩ የሚያደርገው ጠማቂዎቹ ለጠበሉ በተከለለው አጥር ደጃፍ ላይ ከመቆምና የእለቱ ተጠማቂዎች መጠመቅ ከመጀመራቸው በፊት ጸሎት ከማድረግ ያለፈ ቆመው አያጠምቁም።

[14]መረጃ ሰጭ፤ ወ/ሮ አሚና ሁሴን፣ እድሜ 42፣ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ከሎሌ አርሲ ከዲገሉና ጢጆ ወረዳ የመጡ (ቃለ-መጠይቅ፣ ጨፋ ጥር 20/ 2007)፡፡

[15]መረጃ ሰጭ፡- አቶ ገቢሳ ሆርዶፋ፣ እድሜ 59፣ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ፣ በግብርና ስራ የሚተዳደሩ (ቃለ-መጠይቅ ጨፋ 20 2007)።

ከላይ እንደተገለፀው ጠበሎች የሚተዳደሩት በኢ.ኦ.ተ.ቤ ሲሆን የሚገኙትም በቤተ-ክርስቲያናት ቅጥር ግቢ ወይም በዚያው አቅራቢያ ነው። ከመስክ ምልከታ በተገኘው መረጃ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ተጠማቂዎች በአገላለፅ ደረጃ እንደ ኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች "ወደ ጠበል መጣሁ" ሳይሆን "ለመታጠብ መጣሁ" ማለትን ያዘወትራሉ፡፡ ይህ ምንም እንኳዋን ጠበል እንደ ማንኛውም ተራ የምንጭ ውሃ ተደርጎ በሁሉም ተጠማቂዎች ዘንድ የሚታይ ባይሆንም በምእመናን መካከል ያለውን ሃይማኖታዊ ቀኖና ልዩነት ለመጠበቅ ሲባል የተለመደ አባባል ሊሆን ይችላል። ልዩነቱም ክርስቲያንን 'ክርስቲያን' የሚያሰኘው አንዱ ሃይማኖታዊ ቀኖና "ጥምቀት" ከመሆኑ ጋር የአገላለፁ አንድምታ ሊያያዝ ስለሚችል ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ምክንያት የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች "ጠበል ለመጠመቅ መጣሁ" የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ደግሞ "ለመታጠብ መጣሁ" በሚል በውስጥ አወቅ ይገልፁታል፡፡ በሌላም በኩል የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች ሙስሊም ጠበለኞችን "ለምን 'ጠበል ልጠመቅ መጣሁ' አትሉም" በሚል ጥያቄ ወይም ቅሬታ አያነሱም፡፡

አንድ ሰው ለመጠመቅ ወደ ጠበል ሲመጣ የሚከተላቸው ልማዳዊ ደንቦች አሉ። በደንቡ መሠረት ወደ ጠበል ለመጠመቅ የሚመጡ ሰዎች ምንም ዓይነት ምግብና መጠጥ መቅመስ አይኖርባቸውም። ንፅህና አስፈላጊ ነው፡፡ ሴቶች የተለያዩ ተፈጥሯዊ ያልሆኑ መዋቢያ ጌጣጌጥ፣ ለምሳሌ፡-እጅን፣ እግርን፣ ጥፍርን፣ ከንፈርንና ጸጉርን ቀለም መቀባት፤ ሰው ሰራሽ ጸጉር መጠቀም፣ ወዘተ፣ በሁሉም ተጠቃሚዎች ዘንድ እንደ ነውር የሚቆጠሩ ምግባሮች ናቸው። እነዚህን ምግባሮች በሌላ ጊዜ የሚፈጽሙ ቢኖሩ እንኳዋን ወደ ጠበል ሲመጡ ግን ከዚህ ድርጊት በመቆጠብ ነው። አንድ ሰው የሰራውን ወንጀል ወይም መጥፎ ድርጊት፣ ለምሳሌ፡-ግድያን፣ ስርቆትን፣ እና የመሳሰሉትን የፈፀመ ጠበለኛ ሥራውን ደብቆ ለመጠመቅ ቢሻና ቢደፍር በጠበሉ ላይ ያደረው መንፈሳዊ ኃይል ሊያስለፈልፈውና ለጉድ ሊያጋልጠው ይችላል ተብሎ በሁሉም ዘንድ ይታመናል፡፡ ተጠማቂው ይፈራል፡፡ በመሆኑም አስቀድሞ ይናዘዛል።

ተጠማቂዎች የአጠማመቅ ቅደም ተከተል፣ ተከትለው ይጠመቃሉ። በጠበሉ ስፍራ በቀን እስከ 160 ሰው የመጣበት አጋጣሚ እንደ ነበረ ለዚህ ጥናት መረጃ ሲሰበሰብ የተመዘገበ ሲሆን በቦታው ላይ ግን ከህሙማን ልፍለፋ በቀር ሌላ ድምጽ ወይም ወሬ አይሰማም። ተጠማቂዎች እንደ አመጣጣቸው ቅደም ተከተል በቅድሚያ የአርባ አራቱ ተብሎ በሚጠራው የመጠመቂያ ሥፍራ በአንድ ጊዜ ተመሳሳይ ጾታ እስከ አስር ሰው በአንድነት (ያለ ሃይማኖት ልዩነት) ሊጠመቅ ይችላል። ጠበል ለመነከር ሲገባ ተራ አስከባሪ ባይኖርም ጠበለኛው ራሱ እንደ አመጣጡ ተራ ይዞ በመነከር ሙስሊሙም የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች እንደየጾታቸው ሴት ከሴት፣ ወንድም ከወንድ ለየብቻ በተራ በመግባት ይጠመቃሉ።

ጠበለኞች ለመነከር ተራ ሲይዙ ሁሉም ልብስ ስለሚያወልቁና ተደራቢ ልብስ ብቻ ስለሚለብሱ በአለባበስም ሆነ በሌላ ዘዴ የትኛው ሙስሊም የትኛው ክርስቲያን እንደሆኑ አይለዩም። ጠበለኛው የአርባ አራቱን ጠበል ተነክሮ ሲጨርስ ልብሱን ለብሶ ወደ መጀመሪያው ክፍል ወይም

ወደ ጠበሉ ምንጭ በመሄድ የመደብ ቅርጽ ይዞ በተዘጋጀ መሬት ላይ እንደ አመጣጡ ተራ ይዞ ይቀመጣል። በእለቱ በተረኛነት በተመደበ መነኩሴ መሪነት ከ10 እስከ 15ደቂቃ የሚፈጅ የጋራ

ጸሎት ይደረጋል። ጸሎቱም ከመቀመጫ በመነሳት በቁም የሚከናወን ነው። በዚህ ጸሎትም የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች እንደ ኢ.ኦ.ተ.ቤ. ሃይማኖት ተከታዮች ጸሎቱን ከሚመሩት አባቶች ጋር አብረው በመቆም እንዲካፈሉ አይጠበቅባቸውም። ሆኖም ከጥቂቶቹ በስተቀር ጸሎቱ እስኪጠናቀቅ ይቆማሉ።

ጸሎቱ እንደተጠናቀቀ እንደየተራቸው ወደ መጠመቂያው ይገባሉ። ሲገቡም እያንዳንዱ ሰው 0.50ሳ ይከፍላል። ለከፈለ ሰው መከፈሉን የሚያረጋግጥ የገዳሙ ማህተም ያለበት ትኬት ይሰጠዋል። ሳንቲም የለኝም የሚሉም አሉ፤ ሆኖም "ገንዘብ ስለሌለህ አትገባም" አይባልም ይገባል። ግቢ ወስጥ በአንዱ የመጠመቂያ ከለላ ውስጥ በአንድ ጊዜ የሚገባው አንድ ሰው ስለሆነ ሁለተኛው ተራ ይይዛል። በግቢ ውስጥ በአንዴ ከአስር ሰው በላይ አይገባም፤ ግቢው አንሶ ሳይሆን በር ላይ ያሉ አስተናባሪ የወሰኑት ውሳኔ ነው።

ወደ ጠበሉ የመጠመቂያ ግቢ ሲገቡ ማንኛውም ተጠማቂ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች ከሆነ በአንገቱ ላይ ወይም መስቀል ያለበት ክር (ጥቁር ክር ብቻ) ከማሰር በስተቀር ጌጥም ሆነ ልብስ አውልቆ እንደነጠላና ጋቢ የመሳሰሉ ከላይ የሚደረቡ ልብሶችን ብቻ ለብሰው ባዶ እግራቸውን ይገባሉ። አብዛኞቹ ተጠማቂዎች ከእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ውጭ የእለቱ ተረኛ አባት (መነኩሴ) እጅ ወደ ጠበሉ ግቢ ከመግባታቸው በፊት የእጅ መስቀል ይሳለማሉ። የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ወደ ጠበሉ ሲገቡ የሚጮሁና የሚለፈልፉ ቢሆን እንኳዋን እንደ ኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች በመስቀል አይነኩም።

የተለያየ መንፈስ አለብን የሚሉ ህሙማንም ጠበሉ ስር ከደረሱ በኋላ ማንም ሳያስገድዳቸው የሆኑትን ይለፈልፋሉ። በቃኝ ሲሉም በራሳቸው ይነሳሉ። የጠበሉ አወራረድ(ፍሰቱ) ሀይል ስላለው ይሁን በሌላ ምክንያት አንድ ሰው ማንም ሰአት ሳይዝለት ቆየ ከተባለ ከ10-15 ደቂቃ ነው። ከተጠማቂዎች አብዛኞቹ ከተጠቀሰው ሰአት ቀድመው ይወጣሉ።

እያንዳንዱ ሰው ጠበል ለመቅዳት ያመጣውን እቃ በር ላይ ያስቀምጣል። ለመጠመቅ ከሚመጡት መካከል ከ90 እጁ በላይ ጠበል መቅጃ እቃ ይይዛሉ። እቃው ትንሹ አንድ ሌትር የሚይዝ ሲሆን ትልቁ አስር ሊትር የሚይዝ ጀሪካን ነው። ለመጠመቅ ከመጡት መካከል የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ወንድ ልጆች እና ወጣቶች(ሴቶች አይፈቀድላቸውም)ተራቸው እስኪደርስ አንድ ተጠማቂ ተጠምቆ ሲወጣ እየጠበቁ ጠበል ይቀዳሉ። የሚቀዱት ለማን እንደሚቀዱ አያውቁም እቃውን ወስደው ቀድተው በግቢ ውስጥ ይደረድሩታል። ጠበል እንዲቀዳላቸው እቃ ሲያስቀምጡ ሁሉም በየእቃው ላይ የየራሱን ምልክት ያደርጋል። ምክንያቱም በአብዛኛው ተመሳሳይ[16] እቃ ስለሆነ እንዳይቀያየር ነው። ከጠበል አስቀጂዎቹ መካከል "የእከሌ(ቅዱስ/ቅድስት...)ጠበል እንዲቀዳልኝ እፈልጋለሁ" የሚል ካለ

[16] በአብዛኛው የተመለከትኳቸው ቢጫ ቀለም ያለው 3፣5እና ጥቂት 10 ሊትር የሚይዝ ጀሪካን እና አንድ እና ሁለት ሊትር ውሃ ታሽጎ የሚሸጥባቸው በተለምዶ "ሀይላንድ" የሚባሉ ፕላስቲኮች ናቸው።

ከአጥር ውጪ ሆኖ ለመቅዳት የሚገባውን የማንን ጠበል እንደሚፈልጉ ይነግሩታል። ጠበል የተቀዳላቸው ተጠማቂዎች ተጠምቀው ሲወጡ ጠበላቸውን ይዘው ይሄዳሉ። ጠበል ለመጠመቅ ብቻ የሚመጡ ግለሰቦች አሉ። ጠበል የሚጠጣ ከቅርብም ከርቀትም የሚመጣ[17] ማንኛውም ሰው ልክ እንደ መጠመቁ ከዋኔ ሁሉ ንጹህና ባዶ ሆድ ሆኖ መምጣትን የሚጠይቅ ወይም የግድ የሚል ነው።

ጠበል በሚጠመቁበት ጊዜ የህመማቸው ምክንያት ምን እንደሆነ የሚለፈልፉ በርካታ ናቸው። በጣም ስለሚጮሁ የሚናገሩት እያንዳንዱ ከግቢው ውጭ ጭምር ይሰማል። እነዚህ ተጠማቂዎች በአብዛኛው ከጠበሉ መጠመቂያ ሲወጡ መለፍለፋቸውን ያቆማሉ። ከወጡ በኋላም ምን እንደተናገሩ በተለያየ ዘዴ ቃለመጠይቅ ቢደረግላቸውም ምን እንደተናገሩ አያውቁም። ሌላው ሰውም ሆነ እነዚህ ተጠማቂዎች እላያቸው የሰፈረ መንፈስ እንደሚናገር ያምናሉ።

የአጠማመቅ ከዋኔው የተለመደ የጊዜ ወሰን ወይም ገደብ አለው። ይህም በአብዛኛው ከጠዋቱ አንድ ሰዐት ጀምሮ ቢበዛ እስከ ስድስት ሰዐት ድረስ ይካሄዳል፡፡ በምልከታ በተገኘው መረጃ የጠበሉ ስፍራ ላይ የሚሰራ ስራ ለምሳሌ አጥር መጠገን፣ ወደ ጠበሉ ግቢ ሲገባ በሩ ላይ ወንዝ ስላለ መሻገሪያ ድልድዩን መጠገን ችግኝ መትከል የመሳሰሉ ስራዎች ይሰራሉ። ስራውን የሚሰሩት አቅም ያላቸው ጠበል ተጠማቂዎች ሲሆኑ እነሱም ከመጠመቃቸው በፊት እንዲሰሩ ይደረጋል[18]።

በዚህ መልኩ አብዛኛው ሰው ሶስት፣ ሰባት አንዳንዶቹ አስራ አራት ቀን በተከታታይ ይጠመቃሉ። የቀኑን ብዛት ለምን ሁለት አራት ወይም ስድስት አልሆነም ሲባሉ "ህመሙ ጠንከር ያለ ካልሆነ በሶስት ጠንከር ያለ ህመም ከሆነ ሰባት በሌሎች ድጋፍ የመጡ ከሆነ ደግሞ አስራ አራት ቀን መጠመቅ ያድናል።" ከማለት ያለፈ የቁጥሮቹን ትርጉም አያብራሩም።

ተጠምቀው ሲጨርሱ ልብሳቸውን ለብሰው ከገዳሙ ክልል ውጭ ይወጣሉ እንጂ ጠበሉ አጥር ግቢ ውስጥ አይቆዩም ከግቢው ውጭም ቢሆን የሚቀመጥ የለም። ለማረፍና የበል ለመጠጣት የፈለጉ ከገዳሙ ክልል ውጭ ባለ ሜዳ ላይ ያርፋሉ። አብዛኛው ተጠማቂ ከጥምቀቱ በኋላ ከጠበሉ ክልል ውጭ ባለ ሜዳ ላይ በመቀመጥ በየራሱ እቃ የቀዳውን ይጠጣል። ለጠበሉ ተብሎ በተከለለ ግቢ ውስጥ ጠበል መጠጣት አይፈቀድም። "በብዛት መጠጣት ለህመምተኛው በሆድ ውስጥ ያለን በሽታ ይዞ ይወጣል" በሚል አብዛኛው ሰው እስከ ስምንት ሌትር ለመጠጣት ይሞክራል።

[17] በጠበሉ ስፍራ በመገኘት እንደተረዳሁት ጠበሉን ብለው የመጡት ከሩቅም ከቅርብም ሲሆን ለምሳሌ ከባሌ ክፍለ ሀገር፣ ከሽርካ ወረዳ፣ ከዲገሉና ጢጆ ወረዳ፣ ከአሰላ ከተማና ዙሪያው ካሉ የገጠር ቀበሌዎች፣ የሄዱ ጠበልተኞች ነበሩ። ጠበልተኞች የመጡበት ርቀት ሩቁ 400 ኪ.ሜ ሲሆን ቅርብ የሚባለው ደግሞ3 ኪሎ ሜትር ነው።

[18] በጠበሉ ዙሪያ የሚገኘው ደን የለማው በጠበልተኞች የህብረት ስራ ሲሆን ጠበሉ ከመከለሉ በፊት አሁን ያለው ደን አልነበረም።

የጨፋ ጠበል በየእለቱ የተለያዩ ሰዎች ከሩቅም ከቅርብም በመምጣት ከህመማቸው ተፈውሰውበታል፤ እየተፈወሱም ይገኛሉ በማለት ያስረግጣሉ። የጠበል ስፍራው በአመት ሁለት ጊዜ ይዘጋል።"[19] ከጥር እስከ ሰኔ ባሉት ወራት በቀን እስከ 150 ሰው ከእነዚህ ወራት ውጪ ከ50 እስከ 60 ሰው እንደሚጠመቅ ይናገራሉ። በዚህም ጠበል ፈውስ ያገኙ ብዙ ሰዎች እንደሆኑ የገዳሙ መነኮሳትም ሆኑ ከደዌያቸው የዳኑ ግለሰቦች ምስክርነት ይሰጣሉ። አንድ ጊዜ ወደ ጠበሉ መጥተው የዳኑ ለሌሎች ሰዎች ይነግራሉ። እነሱም ይመጣሉ። በዚህ መልኩ ስለ ጠበሉ መረጃ ይለዋወጣሉ። በዚህ ምክንያት በየአመቱ የጠበሉ ተጠቃሚ ቁጥር እየጨመረ ሄዷል። ከህመም ከዳኑ በኋላም በተወሰነ ጊዜ ልዩነት የሚጠመቁ አሉ። በተለይ በጳጉሜ ወር "ጠበሉ የመፈወስ ሀይሉ ይጨምራል" ተብሎ ስለሚታመን ያልታመመው ሰው ጭምር ይጠመቃል።

## 4. ማጠቃለያ እና ይሁንታ

### ማጠቃለያ

ከላይ በቀረቡት ገለጻ በመነሳት ዋና ዋና የፎክሎር ገጽታዎችን በማስታወስ እናጠቃልለዋለን። ይህ ጥናት ያተኮረው በጨፋ ጠበል ፎክሎራዊ ክዋኔን ብቻ የሚመለከት ነው። የሌሎችን የጠበል ስፍራዎች ተሞክሮ አይመለከትም። የጨፋ ወይም የጎንዴ ጠበል የአስታጥቄ ምንጭ ተብሎ የሚጠራእና ለመጠጥና ለሌላም ግልጋሎት ይውል የነበረ የውሃ ምንጭ ነበር። ሆኖም ከ1986 ግንቦት12 ጀምሮ የጎንዴ ወይም የጨፋ ጠበል በመባል ይታወቃል። አንድ የነበረው ምንጭም በዙሪያው የተለያዩ ምንጮች በመፍለቅ በቁጥር አርባ አራት ደርሰዋል። አርባ አራቱም ምንጮች በኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ደንብ መሠረት መጠሪያ አላቸው። በቃላዊ ትረካው መሠረት ዛሬ የጠበል ስፍራ የሆነው ስፍራ ቀደም ሲል አህመድ ግራኝ አውድሞት እንጂ ገዳም ነበር ይላል። ይሄን ትረካ መነሻ በማድረግም ወደ ቀድሞ ገዳምነቱ ለመመለስ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል። አሁንም በመከናወን ላይ ነው። "ጠበል ነው" ከተባለ ጊዜ ጀምሮ በየእለቱ የተገልጋዩ ቁጥር እየጨመረ ሄዷል። በጠበሉ የሚገለገሉት የእስልምና እና የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። በጠበሉ የሚገለገሉት የሁለቱ ሃይማኖት ተከታዮች ያድነኛል የሚለው እምነታቸውና በጠበል መጠመቅ ሂደት ውስጥ የሚያደርጉት ክዋኔ ልዩነት የለውም።

በጠበል የሚገለገሉት ሰዎች ከሃይማኖታዊ ቀኖናው ይልቅ ባህላዊ የሆነው ልማድ ይገዛቸዋል። ለዚህም ማሳያው የህመም ዓይነቶችን በጠበል የሚድኑ እና የማይድኑ ብሎ መፈረጅ ጠበል ሊጠመቁ ሲመጡ የጠበል ምንጮቹ የተለያዩ ስለሆኑ በእጣ መለየት፣ ለመጠመቅ የሚታዘዘውን ደንብ ከሃይማኖት መሪዎች ወይም መምህራን ይልቅ ወደ ጠበል ከመምጣታቸው በፊት በአካባቢው ወደጠበል አዘውትሮ ከሚሄዱ ግለሰቦች መጠየቅ፣ "ብዙ ጠበል መጠጣት ያድናል" ብሎ ማመን እንደምሳሌ ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው።

---

[19]ለፍልሰታ ጾምከነሀሴ 1 እስከ 16፣ ለ16 ቀናትና በሰሙነ ህማማት ለሰባት ቀናት የሚዘጋበት ምክንያት "በግራኝ አህመድ ጦርነት ብዙ እናቶችና አባቶች በዚህ ቦታ ስላለቁ ያለቁትን እናቶች ለማሰብ ሲሆን፤ በሰሙነ ህማማት ያለቁትን አባቶች ለማሰብ ነው ይላሉ። የመረጃ ምንጭ፡- እማሆይ ሳህለማርያም፣ እድሜ 64 (ቃለ-መጠይቅ ሚያዝያ 22/2006 ዓ.ም)።

የውሀ ምንጩ ከተራ ውሃነት ወደ ተቀደሰ ውሃነት የተቀየረው በራእይ አማካይነት ነው። ራእይ አንዱ የሚት ጥናት ትኩረት ነው። ከራእዩ ተረኩ ተገነባ። ተረኩ እምነትን መሠረተ። "ውሃው በፈጣሪ የተመረጠ እና ለመድሀኒት የሚሆን ነው" የሚለው እምነት እንጂ ሳይንስ ወይም በማስረጃ የሚረጋገጥ አይደለም። ይህ ራእይ እንዲሁም ትረካ ለአማኙ ማህበረሰብ የተቀደሰ ትረካ ይሆናል። ለአጥኚዎች አንድ ሚታዊ ትረካ ነው። ለማያምንበት ደግሞ እንደ አተያዩ የተለያየ ትርጉም ወይም ሀቲት ሊሰጠው ይችላል። "የተቀደሰ ትረካ ነው" የሚሉ ማህበረሰቦች የዚህ ጥናት ተተኳሪ ቡድኖች ናቸው።

ትረካው በቃል አንዱ ለሌላው እየነገረ እምነቱ እየሰፋ የጠበል ተጠማቂው ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ፣ እያንዳንዱ የጠበሉ ተጠማቂ ስለ ጠበሉ በተለይ ከህመሙ ስለማዳኑ የሚተርካቸው ግለ ታሪኩ (ጠበል ያድናል የሚለው) እምነት የሚተክሉ ትረካዎች ናቸው።

በትረካው መሠረት የሃይማኖት ተቋሙ (የኢ.ኦ.ተ.ቤ) እየደረጀ ምንም ቤተ-ክርስቲያን ያልነበረበት ቦታ ሁለት ቤተ-ክርስቲያን ተሰርቶ፣ አንድ ገዳም እንዲገደም መነሻ ሆኗል። ቦታው ከእርሻ መሬት፣ ከከብት ግጦሽነት ወደ ተቀደሰ ስፍራ ተሸጋግሯል። ቀድሞ ሰውም ከብትም እንደ ልብ በፈለገው ሰአት ውሀውን ይጠጣ ይታጠብበት ነበረ። አሁን ግን እምነቱ ለጠበል በሚፈቅደው ደንብ ብቻ ይገለገሉበታል። እምነቱ በሃይማኖት አስተምህሮ ላይ ብቻ የተመሠረተ አይደለም። አስተምህሮው በአንድ የሃይማኖት ተቋም ማለትም በኢ.ኦ.ተ.ቤ መሠረት ያደረገ ቢሆን ኖሮ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የጠበሉ ተገልጋዮች እንዲሆኑ የሃይማኖቱ ዶግማና ቀኖና አይፈቅድላቸውም። ሆኖም እምነት ሃይማኖትን ብቻ መሠረት የሚያደርግ ባለመሆኑ አንዱ የፎክሎር የጥናት መስክ ለመሆን አስችሎታል።

ተጠማቂዎቹ ሃይማኖታቸውን መሠረት ሳያደርጉ በልማድ ብቻ ደንብ አውጥተውለታል። ጠበል ለመጠመቅ እንደ ነውር የሚቆጠሩ ምግባሮች ሃይማኖታዊ ደንብ ሳይሆን ሰዎች የተቀደሰ ስፍራ ስለሆነ ካላቸው አክብሮተ የተነሳ ያወጧቸው የተለመዱ ደንቦች ናቸው። በጠበል የሚድን ህመም እና በህክምና የሚድን በሽታ። ጠበል በመነከር እና በመጠጣት የሚድን በሽታ በሚል መፈረጅ። የመጠመቂያ ቀናት፤ ካልተቻለ ሶስት ቀን ወይም ሰባት፣ ከተቻለ አስራ አራት ወይም ሀያ አንድ ቀን እያለ ቀኑ በጨመረ ቁጥር ከህመሙ የመዳን እድሉ እንደሚጨምር ማመን ልማዳዊ እንጂ ሃይማኖታዊ እውቀት ላይ የተመሠረተ አይደለም።

የጠበል ስፍራ ተቀደሰ እንደሆነ በተጠቃሚዎቹ ይታመናል። ይህን የተቀደሰ ስፍራ እና ውሃ ወይም ጠበል በዶግማ ከማይገናኙ የሃይማኖት ተከታዮች አብረው ያለ ልዩነት ይገለገሉበታል። ሆኖም ከዚህ ቀላል የሚባል የማይጋሯቸው ለምሳሌ እንደ መቃብር ስፍራ ያሉትን ስንመለከት ጠበል መነከር ወይም የጠበል ስፍራዎች የሃይማኖት መቻቻል መገለጫዎችም ናቸው።

ለጠበሎች ስፍራ የሚሰጥ ስም ሃይማኖታዊ መሰረት ያለው አይደለም። ለጠበሉ ስፍራ የተሰጠን መጠሪያ ስም በራሱ አንዱ የፎክሎር የጥናት ትኩረት የሚሆን ነው። በጥቅሉ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በጠበል ምክንያት የተገናኙ ማህበረሰቦች እምነት፣ አተያይ፣ ሃይማኖት ያልገደበው ማህበራዊ መስተጋብር የሚታይበት ነው።

**ይሁንታ**

አጥኚዋ በዚህ ጥናት ውስጥ ካሰፈረችው መረጃ በመነሳት ለቀጣይ ቢደረግ መልካም ነው የምትለውን የይሁንታ ሀሳብ እንደሚከተለው ትጠቁማለች።

1. በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የጠበል ቦታዎች የጠበል እሳቤ እንዲሁም የአጠማመቅ ክዋኔው ተጠንቶ ፎክሎራዊ መልኮች ቢለዩ የማህበረሰብ አንድነትን የሚያጠናክሩ ባህላዊ እሴቶች ይኖሩታል።

2.የታሪክ ወይም በተያየዥ የሙያ መስክ ያሉ አጥኚዎች የመካከለኛው ዘመን አሻራ ናቸው የተባሉትን አጽሞች የድንጋይ ላይ ጽሁፍ(ምልክቶች)፣ የተገኙ ንዋየ ቅድሳት ላይ ጥናት ቢደረግ።

3. የመካከለኛውን ዘመን የታሪክ ዐሻራ ይዞ የተገደመው ገዳም እና የፈለቀውን ጠበል ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን አንድ ተቋም ነው፡፡ ስለዚህ ለ"ጨፋ መድሀኒዓለም ደብረቁስቋም፣ ቅድስት ማርያም ወሰሎሜ አንድነት ገዳም" መገደም ምክንያት የሆኑትን የእማሆይ የሺ ሀረግ የህይወት ታሪክ ማስረጃዎቹ ከመደብዘዝና ከመረሳታቸው በፊት ተጠንቶ በጽሁፍ የሚሰፍርበትን መንገድ ቢያመቻች።

## ዋቢ ጽሁፎች


Dundes, A. 1965.*The study of Folklore*, Prentice-Hall, Inc, ENgle wood, cliffs, N.J.

___________ 1976. *Projection in Folklore: A Plea for Psychoanalytic Semiotics. Modern Language Notes* 91:1500–1533.

Fennegan, R. 1992. *Oral tradition and verbal arts,* International Thomson publishing Company. London.

Kalkelachew Ali. 1997. "Religion, Rituals and Mutual Tolerance in Wollo," M.A. Thesis, Department of Sociology and Social Anthropology, Addis Ababa University.

Kothari, C.R. 2004. *Research Methodology*, New age international publishers, Newil. New York.

Segal A. 2004. Very short Introductions; oxfored university press.

ማዕከላዊ እስታስቲክስ ኤጀንሲ። 2002። የ1999ዓ.ም የኢትዮጵያ ህዝብና ቤት ቆጠራ፤ ዐዲስ አበባ።

ወርቁ ከተማ። 2000። "የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ፣ የጨፋ መድኃኒዓለም፣ ደብረ ቁስቋም፣ ቅድስትማርያምና ቅድስት ሰሎሜ የሴቶች አንድነት ገዳም፣ አመሠራረት ፎክሎራዊ ገጽታ።" ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ፣ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፤ የኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር የድህረ ምረቃ ፕሮግራም፣ ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዴሚ። 2006። የአማርኛ መዝገበ ቃላት። ዐዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ማተሚያ ቤት። ዐዲስ አበባ።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን። 1988። መርሐጽድቅ ባህለ ሃይማኖት። ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት። ዐዲስ አበባ።

ደስታ ተክለ ወልድ። 1962። *ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፤* አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት። ዐዲስ አበባ።